# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

## ከዲሴምበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2022
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


ርዕስ ..... i
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ..... 1
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... 2
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ..... 3
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ..... 4
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ..... 4
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ..... 5
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... 5
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... 5
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ..... 6
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... 6
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... 6
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ..... 7
ሁኔታ አዝማሚያ ..... 7
ከዲሴምበር 21-31 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ ..... 7
ከዲሴምበር 21-31 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... 7
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... 8
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... 9


## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት የዲሴምበር ሁለተኛዉ አስር ቀናት በመጀመሪዎቹ አምስት ቀናት ላይ ወደ ሀገራችን ከገባዉ ዕርጥበት ከተፈጠረዉ የደመና ሽፋን በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብና የመካከለኛው ሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፈሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የለሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ በተለያዩ ቀናት ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነት ያህል በአደሌ 3.0 እና 4.3፣በጅግጅጋ 2.4 እና2.8፣ በደብረብርሃን 4.0፣በቡኢ3.4፣ 3.6 እና 4.4፣በአርሲ ሮቤ 3.5፣ 4.2፣ 4.4 እና 4.5፣ በባሌ ሮቤ 4.2፣ በሀሮማያ 2.6፣2.8፣3.2 እና 3.6፣በጨፋ 4.8፣በወገል ጤና 4.2 እና 4.5፣ በመሃል ሜዳ 3.5፣ 4.0 እና 4.5፣ በዳንግላ 4.5፣ በደባርቅ 4.0፣ 4.2 እና 4.5 እንዲሁም በእነዋሪ 4.5 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከአማራ የደብረማርቆስ፣ የደባርቅና የነፋስ መውጪያ ጣቢያዎች፤ ከኦሮሚያ የኢሉአባቦራ፣ የቡኖ በደሌ፣ የጂማ፣ የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቦታዎች ላይ ከ 5-75 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-5 ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከአማራ የደብረማርቆስ፣ የደባርቅና የነፋስ መውጪያ ጣቢያዎች፤ ከኦሮሚያ የኢሉአባቦራ፣ የቡኖ በደሌና የጂማ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቦታዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ቀሪዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅና ነፋሻማ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3) ።


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የዲሴምበር ሁለተኛው አስር ቀናት የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብና የመካከለኛው ሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት  ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመጠን አነስተኛ ቢሆንም በደቡብ አጋማሽ ለሚገኙ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ ጎን ነበረው፡፡ከዴሴምበር መጀመሪዎቹ አምስት ቀናት በኋላ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የተስተዋለ እንደነበር የተተነተኑ የሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ መኸር አብቃይ በሆኑት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመካሄድ ላይ ላለው የሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከደረቃማውና ከነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አይሎ ነበር የተስተዋለዉ ከቅዝቃዜው መጨመር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል(ካርታ 4) ፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የዲሰምበር ሁለተኛው አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረውን ገፅታ ስንመለከት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ያመዘነ ሲሆን፤ በጥቂት የላይኛዉ ባሮ አኮቦ እና በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ እንዲሁም በጥቂት የመካከለኛው አባይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸዉ (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ በሰሜን ንፍቀ ክበብ ከሚገኘው ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ሰፍኖ የሚቆይ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከሞላ ጎደል ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በአረብ ባህር ሰላጤ እየተፈጠረ ያለው ዝቅተኛ የአየር ግፊት ወደ ሀገራችን እርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ እንዲገባ አስተዋጽዖ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የደመና ሽፋን የሚጨምር ሲሆንና አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀላል ዝናብ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚሁ መሰረት ከኦሮሚያ ክልል የኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ አርሲ፣ የጅማ፣ምዕራብ ሸዋ፣ ሰሜንና ደቡብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም፣ በደቡብ ጎንደር፣ በሰሜንና በደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በሸካ፣ ከፋና ቤንቺማጅ ዞን በአብዛኛዎቹ ቦታዎች ላይ እንዲሁም በሲዳማና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ ሆነው ይቆያሉ።




ከዲሴምበር 21-31 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ከዲሴምበር 21-31 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የዲሴምበር ወር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች የሰብል ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚከናወኑበት ወቅት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ጥንካሬ የሚያይልበት ወቅት ነው።

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት የዲሴምበር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው የአገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ሰፍኖ የሚቆይ ሲሆንና፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከሞላ ጎደል ቀጣይነት ይኖረዋል። የሚጠበቀው ደረቃማው የአየር ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ ጠቀሜታ ቢኖረውም፤ ከደረቃማውና ከነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ቅዝቃዜው በቀጣይነት እንደሚስታዋል የትንበያ መረጃዎች አመልክተዋል። ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ጨርሰው ባልተነሱ ሰብሎች፣ በቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚኖረውን ቅዝቃዜ ለማሻሻል የሚረዱ የተለመዱ ተግባራት ለማከናወን የበኩላቸውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራሉ። በሌላ በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የደመና ሽፋን የሚጨምር ሲሆንና አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በተለይም በተወሰኑ የመካከለኛው፣ የምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብና የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ መጠነኛ የእርጥበት መጨመር ሊኖር እንደሚችልና ወቅታቸው ያልሆነው የሰሜን ምዕራብና የምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀላል ዝናብ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህም ሊገኝ የሚችለው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታ ቢኖረውም የሰብል ስብሰባቸውን ባላጠናቀቁና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን እያከናወኑ በሚገኙ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ በግብርና ተግባር ላይ የጎላ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ተብሎ ባይታሰብም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ግን መጠነኛ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ስለሚችል ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም አርሶ አደሮች በየጣልቃው የሚኖረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን በአግባቡና በጊዜው እንዲሰበስቡና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን በተገኘው አጋጣሚ እንዲያከናውኑ ይመከራሉ።

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ  እና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ተፅዕኖ ስር የሚቆይ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በደቡብ  የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከነዚህም መካከል በላይኛው እና በመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ በጥቂት አባይ፣ በመካከለኛው እና በታችናው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት በላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ትንበያው ይጠቁማል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛዉ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡